የሰበር መ.ቁ. 36692

ጥቅምት 25 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብድልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መሰሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** አንበሳ የከተማ አውቶቡስ አገልግሎት ድርጅት

ነገረፈጅ ፋሲካ በለጠ - ቀረበ

**ተጠሪ፡-** ተስፋዬ መኰንን - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሠሪና ሠራተኛ ሕግ የሚታይ የስራ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ ሲሆን፣ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተው ከሐምሌ 1 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ ለድርጅቱ ሠራተኞች በሙሉ የአንድ እርከን የደመወዝ ጭማሪ ተደርጎአል፡፡ እኔም የድርጅቱ ሠራተኛ በመሆኔ ጭማሪው ሊሰጠኝ ሲገባ አለአግባብ ተከልክያለሁ፡፡ ስለዚህም ጭማሪ እንዲሰጠኝ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡ አመልካች ደግሞ ለክሱ በሰጠው መልስ ከሣሽ ሦስት አራተኛውን ጊዜ በስራ ላይ ስላልነበረ ጭማሪውን ሊያገኝ አይችልም በማለት ተከራክሮአል፡፡ ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ የግራ ቀኝ ወገኖችን ክርክር የመረመረ ሲሆን፣ በመጨረሻም የአመልካችን ክርክር ባለመቀበል ተጠሪ በጠየቀው መሠረት የደመወዝ ጭማሪው ይሰጠው በማለት ወስኖአል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በተመሣሣይ ሁኔታ ወስኖአል /የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶአል/፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች መጋቢት 22 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በድርጅቱ ፀንቶ ያለው በሕብረት ስምምነት ጭማሪው የማይደረግበትን ምክንያት አስቀምጦአል እየተባለ አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ ሕጋዊ የሚሆንበት አግባብ ምንድነው? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ነጥቡን ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሁለቱ ወገኖች ክርክር እና በሥር ፍ/ቤቶች ከተሰጡት ውሣኔዎች ይዘት መገንዘብ እንዲቻል ነው ተጠሪ በተባለው የበጀት ዓመት ውስጥ የዓመቱን 3/4 /ሦስት አራተኛ/ ጊዜ በስራ ላይ አልነበረም፡፡ በወቅቱ ፀንቶ በነበረው /ባለው/ የህብረት ስምምነት አንቀጽ 29/5/ እንደተመለከተው ይህን ያህል ጊዜ በስራው ላይ ያልተገኘ ሠራተኛ ጭማሪው እንደማይሰጠው ደግሞ አላከራከረም፡፡ የስር ፍ/ቤቶች ይህንኑ በሚገባ ስለመገንዘባቸው በውሣኔዎቻቸው ላይ የገለፁ ሲሆን፣ ጭማሪው መሰጠት አለበት በማለት የወሰኑት ግን በሕብረት ስምምነቱ የሌለን ምክንያት መሠረት በማድረግ እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡ ይህ ተጠሪ አመልካች በወሰደው የስራ ውል ማቋረጥ እርምጃ ምክንያት በክርክር ስለመቆየቱ የሚገልጽ ነው፡፡

በእርግጥም አመልካች የስራ ውሉን አቋርጦ ስለነበር ተጠሪ ለፍ/ቤት ባቀረበው ክስ መሠረት ክርክር ከተደረገ በኂላ ወደስራው እንዲመለስ ተወስኖለታል፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ይህንኑ ሁኔታ ለእርከን ጭማሪው እንደበቂ ምክንያት አድርገው የወሰዱት ተጠሪ በስራው ላይ ሊገኝ ያልቻለው አመልካች በወሰደው ሕገ ወጥ የስራ ውል ማቋረጥ ምክንያት ነው፡፡ ይህንኑም በፍ/ቤት ተረጋግጦ ተወስኖአል በማለት ነው፡፡ በበኩላችን እንደምናየው የእርከን ጭማሪ አሰጣጥን በተመለከተ የተደነገገው የሕብረት ስምምነቱ አንቀጽ 29/5/ በግልጽ የሚያመለክተው በበጀት ዓመቱ ውስጥ 3/4ኛው ጊዜ በስራ ላይ ያልተገኘ ሠራተኛ የእርከን ጭማሪ የማይሰጠው እንደሆነ ነው፡፡ ድንጋጌው ይህን ያህል ግልጽ ከሆነ ደግሞ ትርጉም የሚያስፈልገው አይሆንም፡፡ አመልካች የስራ ውሉን ያቋረጠው ሕገወጥ በሆነ ምክንያት ነው ወይስ አይደለም? በሚል ጭብጥ ላይ ተመስርቶ ተሰጥቶ የነበረው ውሣኔም ለተያዘው ክርክር አወሳሰን ተገቢነት ያለው አይደለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የጠየቀውን የእርከን ጭማሪ ሊያገኝ ይገባል ብሎ ለመወሰን የሚያስችል የሕግ ምክንያት የለም፡፡ ከዚህ የተነሣም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 34178 በታህሣሥ 14 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 63056 የካቲት 7 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. ተጠሪ በክሱ የጠየቀውን የአንድ እርከን የደመወዝ ጭማሪ እንዲያገኝ የሚደረግበት የሕግ ምክንያት የለም በማለት ወስነናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ